SmaRT Ethiopia

INITIATIVE ON Sustainable Animal Productivity

CGIAR



Photo ILRI/Mesfin Mekonnen

# የእንስሳት ጤና | ማህበረሰብ አቀፍ የበጎችና የፍየሎች የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ ቁጥጥር

## ቁልፍ መልዕክቶች

- የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ (gastrointestinal tract parasites) በኢትዮጵያ ውስጥ ለትናንሽ አመንዣኪ የቤት እንስሳት (በጎችና ፍየሎች) ምርታማነት መቀነስ በዋናነት አስተዋፆ አላቸው:: ስለሆነም የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች መውሰድ በእንስሳቱ ላይ የሚያደርሱትን የጤና እክሎችም ሆነ ይህንን ተከትሎ የሚመጣውን የገበሬዎችን እና የአርብቶ አደሮችን የኢኮኖሚ ድቀት ማስቀረት ወሳኝ ተግባር ነው::
- የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ በጎች እና ፍየሎች ላይ በምን ምክንያት ሊከሰቱ እንደሚችሉ፣ ምልክቶቹ ምን እንደሆኑ፣ ሕክምናው እንዴት መሰጠት እንዳለበት እና እንዴት መቆጣጠር እና መከላከል እንደሚቻል ለልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ለእንስሳት መድሐኒት ቤት ባለቤቶች፣ ለማህበረሰቡ እና ለእንስሳት ጤና ሠራተኞች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት በዚህ ረገድ ያላቸውን እውቀት ማሳደግ ውጤታማ መንገድ ነው:: ስልጠናውን የወሰዱ ሰዎች ያገኙትን ዕውቀት ስልጠናዎችን በመስጠትና በማህበረሰብ ውይይት አማካኝነት ለእንስሳት አርቢዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ::
- የጋራ የግጦሽ መሬቶች በበሽታው ለመያዝ ዋናዎቹ መንስኤዎች ናቸው:: ስለሆነም የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተሕዋሲያንን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ማሕበረሰብን መሰረት ያደረገ አሠራር መከተል አስፈላጊ ነው::
- የጥገኛ ተዉሳክ ቁጥጥር ፕሮግራም በሚሳተፉ ቤተሰቦች ያስገኘውን ለውጥ ለመከታተል መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል:: የሚሰበሰቡ መረጃዎች የእንስሳቱን ጤንነት እና አፈፃጸም የሚያመላክቱ ሲሆን የሰውነት ሁኔታን፣ የደም ማነስ ምርመራ ነጥብ (FAMACHA score/anemia guide)፣ የሰውነት ክብደት፣ የታመቀ የቀይ ደም ሕዋስ መጠን (packed cell volume) እና በእንስሳቱ በጠጥ ላይ በሚታዩ እንቁላሎች ብዛት መሆን ይገባዋል::
- በአራት ቦታ ላይ የተካሄደው ጥገኛ ትላትሎችን ከእንስሳቱ ላይ የማስወገድ ፕሮግራም በበጎች እና ፍየሎች የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክን እና በበጠጣቸዉ ላይ የሚታዩ እንቁላሎች ብዛት በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል:: ቀጣይነት ያላቸው እና ስልታዊ የሆኑ የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክ ለማጥፋት የሚረዱ መድሃኒቶችን (anthel-mintic) ድቡልቡል ትልና ፊጌን (nematode) ፣ ክር ቅርጽ ትሎችን (tread worms) እና በ‘trematode’ መደብ የሚመደቡ ጠፍጣፋ ትሎችን (flatworms) ለማስወገድ በአመት ሁለት ጊዜ በዝናብ ወቅት መጀመሪያ ላይ መስጠት ተደጋጋሚ የሆነ የበሽታዉ ክስተት እና ስርጭትን ለመከላከል ይረዳል::

## መ ግ ቢ ያ

የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክ የእንስሳቱ በሽታዎች ዋነኛ ምክንያቶች በመሆን ትናንሽ ይዞታ ባላቸው አርቢ ማህበረሰቦች ላይ አውዳሚ የሆነ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ያስከትላሉ:: በኢትዮጵያ በደጋው ክፍል በተደረጉ ጥናቶች በትናንሽ አመንዣኪ የቤት እንስሳት ላይ የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክ ክስተትና በምርት ላይ ባስከተሉት ተጽዕኖዎች ላይ መረጃ ተሰብስቧል:: ጥናቶቹ እንደሚያሳዩት እንደ ድቡልቡል ትልና ፊጌ በመሳሰሉት ትሎች (nem-atode) የበጎች እና የፍየሎች የመያዝ መጠን በአማካይ 75.6% ደርሷል(Asmare et al 2016.)::

እነዚህ ጥገኛ ተዉሳኮች በብዙ ቁጥር በእንስሳቱ ላይ ሲኖሩ ወይንም እንስሳቱ የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘታቸው ወይም በሌሎች በሽታዎች ሲዳከሙ በሽታው ይከሰታል:: በበሽታው የተያዙ በጎችና ፍየሎች የምግብ ፍላጎታቸው እና ንጥረ ምግቦችን የመቀበል ችሎታቸው ይቀንሳል:: ንጥረ ምግቦችን የመቀበል ችሎታቸው ሲቀንስ የደም ማነስ ያስከትላል፣ የማደግ ሁኔታቸውን እና የሚሰጡትን ወተትም ይቀንሰዋል:: በተጨማሪም የጸጉራቸው ሁኔታ ጥሩ አለመሆንን እና የእንስሳቱን ሞት ሊያስከትል ይችላል:: ሆኖም እነዚህ ጥገኛ ተሕዋሲያን የሚያስትሉትን ተፅዕኖ መጠን በቁጥር ለማስቀመጥ ተጨማሪ ጥናቶችን ማድረግ ያስፈልጋል::

በጣም የተለመዱት የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክ

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE

ICARDA Science for resilient livelihoods in dry areas

አይነቶች ኔማቶድስ (nematodes) ወይንም ድቡልቡል ትሎች ሲሆኑ እነሱም በእንግሊዘኛዉ አጠራር ሄመንከስ (Haemonchus)፣ ትራይኮስትሮንጊለስ (Trichostrongylus)፣ ኦሶፋጎስቶመም (Oesophagostomum)፣ ቡኖስቶመም (Bunostomum)፣ እስትሮንጃሎይድ (Strongyloides)፣ ኩፐሪያ (Cooperia) ነማቶዳይረስ (Nematodirus) እና ትሪኩሪስ (Trichuris) ይባላሉ::

የጉበት ትል ማለትም ፋሲዮላ ሄፓቲካ እና ፋሽወላ ጃይጋንትካ (Fasciola hepatica and Fasciola gigantica) ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸዉ ሲሆኑ የህክምና መድሃኒቶች መለማመድ/አለመስራት በየጊዜዉ እየጨመረ ያለ ችግር ሆኖል:: እነዚህ ጥገኛ ተዉሳክን ለመቆጣጠር በተለመዶ በጥቅም ላይ የሚዉሉት ፀረ ጥገኛ ትላትሎች (anthelmintics) መድሐኒቶችን ናቸዉ:: ሆኖም ጥገኛ ተዉሳክን ለማጥፋት የሚረዱ መድሐኒቶችን ገበሬዎችና አንዳንዴም የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሰጭዎች መወሰድ ካለባቸው መጠንና መቆየት ከሚችሉበት ጊዜ አንፃር በትክክል አይጠቀሟቸውም:: ጥሩ ጥራት ያላቸው መድሐኒቶችን ማግኘት አለመቻል ሌላው ተግዳሮት ነው:: ሆኖም መድሐኒቶችን ስልታዊ በሆነና በተመቻቸ ሁኔታ መጠቀም ቢቻል እንኳን ይህ የመቆጣጠሪያ ዘዴ አነስተኛ ይዞታ ላላቸው ገበሬዎች ውድ ሊሆንባቸው ይችላል:: ይህ የመቆጣጠሪያ ዘዴ በጋራ እንስሳትን በማስተዳደር ሥርዓት/የጋራ ግጦሽ የተለመደ በሆነበት በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ ውጤታማ የሚሆነው በከፊል ብቻ ነው::

ስለሆነም የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክን ለመቆጣጠር እና የረዥም ጊዜና ዘላቂነት ያላቸው ውጤቶች ለማምጣት ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች መስራት አስፈላጊ ነው:: ጥገኛ ተዉሳክ በእንስሳቱ አንጀት ውስጥ ስለሚኖሩ እንቁላላቸው በከብቶቹ በጠጥ ውስጥ ይታያል:: በጋራ የግጦሽ መሬት ስርዓቶች እንስሳቱ በአንድ ቦታ ስለሚግጡ እና የጉድጓድ ውሃ አብረው ስለሚጠጡ እና ከሳሩ ጋር የተፈለፈለ የእንቁላል እጭ ወደ ሆዳቸው ስለሚያስገቡ የመተላለፉን ሂደት ቀላል ያደረገዋል::



Photo ILRI/Mesfin Mekonnen

*የዝናብ ወቅት ከመግባቱ አስቀድሞ በመደበኛነት በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረግ ከእንስሳት ላይ ትሎችን የማስወገድ ስራን ማህበረሰቡ በጋራ ሆኖ ማከናወኑ የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተሕዋስያንን ስርጭት ለመቆጣጠር ውጤታማ መንገድ ነው::*

## ፈጠራዉ

ማህረሰብ አቀፍ የበጎች እና ፍየሎች የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተሕዋሲያን መቆጣጠሪያ ፕሮግራም የአንድ ማህበረሰብ አባላት ለሆኑ እና እንሰሶቻቸዉን በጋራ ግጦሽ መሬት ለሚያዉሉ ገበሬዎች የግንዛቤ ማሳደጊያ እና ስልጠና አዘጋጅቷል:: የግንዛቤ ማሳደጊያው እና ስልጠናዎቹ ስልታዊ በሆኑ እና በጊዜ በተለኩ ጥገኛ ተዉሳኮችንን ለማጥፋት በሚረዱ መድሐኒቶችን (anethelmintic) የሕክምና ዘመቻዎች እና መደበኛ ከሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚተገበር የእንስሳት በሽታ ክትትል ጋር ተቀናጅቷል::

ለገበሬዎቹና ለእንስሳት ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚሰጡት ስልጠናዎች የሚያተኩሩት በውስጥ ጥገኛ ተዉሳኮች ዓይነት፣ በሕይወት ኡደታቸው እና የውስጥ ጥገኛ ተዉሳኮችን በመከላል እና በመቆጣጠር ላይ ነው:: ስልጠናዎቹ ስለ ጥገኛ ተዉሳኮቹ ያለው እውቀት አናሳ በሆነባቸው እና በሽታዉ በበጎችና ፍየሎች ምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያስከተሉባቸው ባሉ በደጋማዎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች ነው:: በተጨማሪም ማህበረሰቦቹ ባጋጠሚቸው የተለያዩ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩና በማህበረሰቡ ደረጃ ምን መደረግ እንዳለበት የመፍትሄ ሃሳቦችን እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ:: ከሰለጠኑት ገበሬዎች ውስጥ የተወሰኑ ገበሬዎች በማህበሩ አባላት ተመርጠው ዕቅዶችን እንዲከታተሉ ሀላፊነት ተሰጥቷቸዋል::

ስልጠናዎቹ የተሟሉ እንዲሆኑ ከገበሬዎቹ እና ከአካባቢው የእንስሳት ሐኪሞች ጋር በመሆን በተወሰነ ጣቢያ ላይ አመታዊ ስልታዊ የሕክምና መስጫ የጊዜ ሰሌዳ/ሰንጠረዥ ተዘጋጅቷል:: በዚህም የቤተ ሙከራን በጠጥ ናሙና የጥገኛ ተዉሳክ ምርመራን መሰረት በማድረግ ጥገኛ ተዉሳኮችን ለማጥፋት የሚረዱ መዳሃኒቶችን በዓመት ሁለት ጊዜ ለመስጠት ከስምምነት ተደርሷል:: ለድቡልቡል ትልና ፊጌ ለመሳሰሉት ትሎች (nematode) እንደ አልቤንዳዞሎ የመሳሰሉት ብዙ አይነት ጥገኛ ተዉሳኮችን የሚያጠፉ መድሃኒቶች የሚሰጥ ሲሆን ለጉበት ትል ደግሞ የተወሰነ አይነት ጥገኛ ተዉሳክን የሚያጠፉ መድሀኒቶች ለምሳሌ ትራይክላቤንዳዞል (fascinex) በአንድ ጊዜ ይሰጣል::

የሰውነት ሁኔታ የሚያመላክት ነጥብ (body condition scoring, BCS)፣ የአይን የዉስጥ ክፍል የደም መጠን ውጤት/ነጥብ (FAMACHA score)፣ የሰውነት ክብደት፣ የበጠጥ እንቁላል ቁጥርና (FEC)፣ የታመቀ የቀይ ደም ሕዋስ መጠን (Packed Cell Volume, PCV) ላይ መረጃ ተሰብስቧል:: ይህም ገበሬዎች እና የእንስሳቱ ሐኪሞች የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክን መንጋውን እንዳይበክሉ እና እንዲከላከሉ ከመርዳት በተጨማሪ የሰውነት ሁኔታ ውጤት፣ የአይን የዉስጥ ክፍል የደም መጠን ውጤት፣ የሰውነት ክብደት በበጠጥ ውስጥ ካሉ ጥገኛ ተዉሳክ እንቁላል ቁጥር ጋር ስላላቸው ዝምድና የበለጠ እንዲረዱ ያደርጋል::

## ለፈጠራዉ አስተዋጽኦ ያደረጉ ጉዳዮች

የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ የሚጎዳው የበጎችን እና የፍየሎችን  ጤና ብቻ አይደለም። ቀጥተኛ ባልሆነ ተዘወዋሪ መንገድ የገበሬዎችን እና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮና ጤና በቂ ምግብ በማሳጣትና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በመፍጠር ይጎዳል። በእንስሳቶቻቸው ውስጥ የሚገኙትን ጥገኛ ተዉሳክ በመቆጣጠር ገበሬዎች የምርታማነታቸውን መጠን በመጨመር ገቢ የማግኘት እድላቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ። በመቀጠልም የኑሮ ደረጃቸው ስለሚሻሻል ቤተሰቦቻቸውን በተሻለ ሁኔታ ሊረዱ ይችላሉ።

በተጨማሪም የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ ቁጥጥር ፕሮግራም በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ የረዥም ጊዜ ዕቅድ የሆነውን ማህበረሰብ አቀፍ የእርባታ ስልትን ጭምር ሊያግዝ ይችላል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ጤነኛ የሆኑ እንስሳት ብዙ ዘር ማፍራት ስለሚችሉ ነው።

## ዕድገቱና ተጽዕኖዎቹ

የቁጥጥሩ ፕሮግራም ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ሕዝቦች ክልል እየተተገበረ ቆይቷል። ስልጠናዎቹ የጨጓራና አንጀት ተሕዋሲያንን የመቆጣጠር ዘዴዎችን በተመለከተ የተጠቃሚዎቹን እውቀት፣ አመለካከት እና ልምዶች በማሻሻል ረገድ ስኬታማ ነበር ማለት ይቻላል።

- 60000 በጎች እና ፍየሎች ያላቸዉ ከ4000 የሚበልጡ ገበሬዎች ከአራት ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ተሳታፊ ሆነዋል።
- በማህበረሰብ አቀፍ የእርባታ ፕሮግራም መንደሮች ዉስጥ ተሳታፊ የሆኑ ከአራት ሺህ የሚበልጡ ገበሬዎች እና 36 የእንስሳት ሐኪሞችና ተመራማሪዎች ወቅታዊውን እንስሳትን ከጥገኛ ተዉሳኮች ነፃ የማድረግ ህክምና እና ቅድመ መከላከል ስምምነት በተደረገበት ዓመታዊ መርሐግብር መሰረት  የጊዜ ሰሌዳዉን ጠብቀው ተግብረዋል።
- ሃያ የእንስሳት ሐኪሞች እና 16 ተመራማሪዎች የጨጓራና አንጀት ተዉሳክን እንዴት መመርመርና መቆጣጠር እንደሚቻል ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።
- ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ ያሉት የሥራ አፈፃፀም መለኪያ (የእንስሳቱን ጤንነት እና አፈፃጸም የሚያመላክቱ) መረጃዎች እየተሰባሰቡ ናቸው።

በተሰሩት ሥራዎች ምክንያት የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል ።

- የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ አጠቃላይ ወቅታዊ ስርጭት ቀድሞ ፕሮግራሙ ሲጀመር ከነበረው 54.41% (95% CI: 52.18-56.62) ወደ 44.80% (95% CI 40.00-49.71) ($p<0.05$) ዝቅ ብሏል።
- በአጠቃላይ የጥገኛ ተዉሳክ ስርጭት መጠን እና  በእያንዳንዱ ግራም በጠጥ የሚገኘው አማካኝ የእንቁላሎች ቁጥር ከአመት ወደ አመት እየቀነሰ ሄዷል። ለምሳሌ ያህል በጉበት ትል (liver fluke) የተበከሉ በጎች መጠን ያለማቋረጥ በተሰራው የትሎች ማስወገድ ሥራ ምክንያት በአራት አመታት ውስጥ ከ18.17% ወደ 4.21% ዝቅ ብሏል።
- በብዙዎቹ ጣቢያዎች ከጥገኛ ተዉሳክ ማስወገድ ዘመቻዎች በኂላ አማካኝ የእንቁላል ቁጥር ቅነሳ ከ90% በላይ ሆኗል።
- በእያንዳንዱ ግራም ውስጥ በአማካይ ያሉ እንቁላሎች (EPG) እና የአይን የዉስጥ ክፍል የደም መጠን ውጤቶች (FAM-ACHA) በአዎንታዊነትና በጉልህ ሲዛመዱ ኢ.ፒ.ጂ (EPG) ከታመቀ የሕዋስ መጠን (PCV) እና ከሰውነት ሁኔታ ውጤት (BCS) ጋር ግን በተቃርኖ ይዛመዳሉ። ይህ ውጤት በተሰጡት መለኪያዎች መሠረት በጣም የተጠቁ እንስሳትን መርጦ ለማከም ለሚወጣ እቅድ መሠረት ይሆናል።
- የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተሕዋሲያን ስርጭትና በበጠጥ ውስጥ የሚገኙ እንቁላሎች መቀነስ እንስሳቱ ክብደት እንዲጨምሩ እና ፀጉራቸው እንዲያድግ አስተዋፅዖ አድርጓል።

## ወሳኝ የስኬት ምክንያቶች

የማህበረሰብ አቀፍ የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ መከላከል ፕሮራም ስኬታማ እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ተሳታፊዎች የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ በበግ እና ፍየል ምርትና ምርታማነት ላይ ስላላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ በስልጠናዎችና በማህበረሰብ አቀፍ  ውይይቶች አማካይነት መወያየት እና መማር መቻላቸው ከስኬቱ ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው። ስልጠናዎቹ በጥገኛ ተዉሳክ አይነቶች፣ በሕይወት ኡደታቸውና መከላከልና መቆጣጠር ላይ ያተኮሩ ነበሩ።
- የተገኙት ዕውቀቶችና ምርጥ ተሞክሮዎች በማሕበረሰቡ አባላት መሀል በሚደረግ አቻ ለአቻ ትምህርትና የልምድ ልውውጥ ተጠናክረዋል።
- በብሔራዊ የምርምር አጋሮች የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ የቤተ ሙከራ ምርምር ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። ይህ የተደረገው በምርምር ማዕከላት ቤተ ሙከራዎች ወይንም በክልል የእንስሳት ህክምና ቤተሙከራዎች ውስጥ የቤተሙከራ ትንተና እንዲያካሂዱ፣ ሪፖርት እንዲያደርጉ ብሎም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰተውን የበሽታውን ስርጭት እንዲከታተሉ ለማስቻል ነው።

## አንደምታዎችና ምክረ-ሐሳቦች

- ይህ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ውስጥ የበጎችና ፍየሎች እርባታ ታዋቂ በሆነባቸው ቦታዎች መስፋፋት አለበት።
- የፕሮግራሙን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ገበሬዎች እና የእርባታ የህብረት ሥራ ማህበራት ሙሉ የባለቤትነት ሀላፊነት መውሰድ አለባቸው። ይህን በማድረግ ባለሙያዎች ያወጧቸውን ስልቶች ለረዥም ጊዜ በስራ ላይ ማዋል ይቻላል። ይህንን በተግባር ላይ ለማዋል ከእንስሳት ጤና ባለሞያዎች ጋር መገናኘትን፣ አመታዊ ጥገኛ ተዉሳክን የመከላከል ዕቅድ ማዘጋጀትንና ጥገኛ ተዉሳክን ለማጥፋት የሚረዱ መድሐኒቶችን ማቅረብን ይጠይቃል።
- ገበሬዎች ከብቶቻቸውን ጤነኛ እንዲሆኑ የሚያደርጉትን ጥረት ለመደገፍ በእንስሳት ጤና ላይ የተሰማሩትን የግሉን ዘርፍ ስራው ሊያስገኝላቸው የሚችሉትን የሰራ እድሎች በማሳየት እንዲሳተፉ ማበረታታት ያስፈልጋል።
- የጨጓራና አንጀት ጥገኛ ተዉሳክ ቁጥጥር ፕሮግራም በማህበረሰብ ደረጃ የሚካሄድ የማንኛውም የእርባታ ፕሮግራም ዋነኛ ተግባር መሆን አለበት። በተጨማሪም የመንግስት የእንስሳት እርባታ ኤክስቴሽን ክንፍ የሥራውን ዕቅድ፣ ክትትልና ድጋፍ መምራት አለበት።



Photo ILRI/Mesfin Mekonnen

*የእንስሳት ሐኪሙና መርማሪው የበጠጥ ናሙናና የጨጓራና አንጀት ተዉሳክን መረጃ ሲሰበስቡ*

## ማጠቃለያ

ማህበረሰብ አቀፍ የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ ቁጥጥር የግጦሽ መሬትን እና የውሃ ማጠጫ ቦታዎችን የሚጋሩ፣ ተገቢና ስልታዊ የሆኑ የትሎች የማስወገጃ ስልቶችን የሚጠቀሙ እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ ክትትሎችን በተከታታይ የሚያደርጉ የእንስሳት አርቢዎችን ሙሉ ተሳትፎ ይጠይቃል:: ስለሆነም ለስራው ሀብትን መመደብ፣ ለግብአቶችና ለአገልግሎቶች የተሻለ ተደራሽ መሆንን እንዲሁም ሥራው ዘለቄታዊ እንዲሆን አቅም መገንባትን ይጠይቃል::

ከበጎችና ፍየሎች ወቅታዊ ሕክምና በተጨማሪ የአፈፃፀም መለኪያን በመጠቀም ከተመረጡ እንስሳት ላይ ትሎችን ማስወገድ ጥገኛ ተሕዋሲያንን ለማጥፋት የሚረዱ መድሐኒቶችን መላመድ እንዳይኖር ይከላከላል::

በአጠቃላይ በጎችን በሚያረቡ በኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች የጨጓራና አንጀት ቧንቧ ጥገኛ ተዉሳክ ቁጥጥር የተቀናጀ አቀራረብ ያስፈልገዋል:: ይህ ማለት የአካባቢ (ለምሳሌ ግጦሽ መሬት) አስተዳደር/አጠቃቀምን የሚያካትት እና የጣምራ ህክምና አሰጣጥ ስልትን (combination drug strategy) መጠቀም ያስፈልጋል:: ይህም ጥገኛ ተሕዋሲያን ለመላመድ የሚያደርጉትን ጫና ይቀንሰዋል::

## ተዛማጅ ሕትመቶች


**Report** of community conversations on animal health management https://hdl.handle.net/10568/114132

**Report:** Community based approach for the control of gastrointestinal parasites -https://hdl.handle.net/10568/114324

**Brief:** Community based gastro-intestinal parasite control - http://hdl.handle.net/10568/80975

**Report:** Community conversation on small ruminants gastro intestinal parasite control https://hdl.handle.net/10568/114079
-
Alemu, B., Desta, H., Kinati, W., Mulema, A. A., Gizaw, S., & Wieland, B. 2019. Application of mixed methods to identify small ruminant disease priorities in Ethiopia. Frontiers in Veterinary Science 6. https://doi.org/10.3389/fvets.2019.00417

Asmara, K., Sheferawa, D., Aragawa, K., Mesele, A., Sibhatb, B., Hailec, A., Kiarad, H., Szonyie, B., Skjervef, E., Wieland, B. 2016.

Gastrointestinal nematode infection in small ruminants in Ethiopia: systematic review and meta-analysis. Acta Tropica 160:68–77. https://doi.org/10.1016/j.actatropica.2016.04.016

Gizaw, S., Alemu, B., Desta, H., Asfaw, T., Mersha, T., Mekonnen, M., Arke, A. and Wieland, B. 2021. Community-based approach for the control of gastrointestinal parasites under smallholder sheep farming systems. Nairobi, Kenya: ILRI.

Mekonnen, M., Assefa, A., Nane, T., Ayele, F., Arke, A., Elias, B. 2019. Small Ruminant Health Intervention Calendar in Ethiopia. Nairobi, Kenya: ILRI.


## ምስጋና


ይህ ምርምር፣ ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን (CGIAR)፣ በእርባታ እንስሳት ላይ በሚያካሂደው የምርምር መርሃ-ግብር ውስጥ ሲደረግ ቆይቶ፣ በCGIAR ዘላቂ የእንስሳት ምርታማነት ኢኒሼቲብ ውስጥም ቀጥሏል:: የCGIAR ምርምር የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከCGIAR Trust Fund አስተዋፅዖዎች ነው:: CGIAR የምግብ ደህንነቱ የተረጋገጠበት መጪ ዘመን እንዲፈጥር የሚሠራ ሉላዊ የምርምር ሕብረት ሲሆን፣ በአየር ሁኔታ ቀውስ ውስጥ የምግብን፣ የመሬትን፣ እና የውሃን ሥርዓቶች ለማሻሻል




Photo ILRI/Mesfin Mekonnen

*የእንስሳት ሐኪም፣ ለቤተሙከራ ምርመራ የበጠግ ናሙና ሲሰበስብ*


በቁርጠኛነት ይተጋል:: በተጨማሪም፣ እነዚህ የምርምር ወረቀቶች ወደ አማርኛ እንዲተረጎሙ እና የገፅ ንድፋቸው እንዲሠራ፣ የCGIAR የአየር ሁኔታ ምርምርን ተፅዕኖ ማቀለጠፍ ለአፍሪካ (AICCRA) ለተሰኘው ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገው የዎርልድ ባንክ አካል ለሆነው ዓለም-አቀፍ ልማት ማኅበርም (IDA) ምስጋና እናቀርባለን::


## አጋሮች

ስማርት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) እንዲሁም ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር እንስቲትዩት (NARS) ጋር በመተባበር በዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ ምርምር ማዕከል (ICARDA) የሚመራ ነው::


### ፀሐፊዎች

Mekonnen, M.[1] , Alemu, B.[1] , Gizaw, S.[1] , Desta, H.[1] , Wieland., B.[2] and Knight-Jones, T.[1]

1 International Livestock Research Institute
2 Institute of Virology and Immunology, Switzerland


## ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት


*መስፍን መኮንን*
Mesfin Mekonnen · M.Mekonnen@cgiar.org
Animal Health Research Associate
ILRI, Addis Ababa, Ethiopia



*ይህን ህትመት ለመጠቀም ፍቃድ የሚሰጠው the Creative Commons Attribution 40 በተባለ ዓለም አቀፍ ፈቃድ ሰጭ በኩል ነው:: ኦክቶበር 2021*